# ለምን የኮቪድ-19 ክትባት ማግኘት አለብኝ?

## ምክንያቱም ውጤታማ ስለሆነ

በእድሜ፣በዘር፣በፆታ እና በጤና ሁኔታ የሚለያዩ 40,000 ሰው ባሳተፉ የክሊኒካል ሙከራዎች ላይ የ Pfizer እና Moderna ክትባቶች ኮቪድ-19ን ለመከላከል ከ90% በላይ ውጤታማ ሆነዋል። ክትባቶቹ በህይወት ያለ የቫይረስ ህዋስ የሌላቸው ሲሆን በኮቪድ-19 ሊበክልዎት አይችልም።

## ምክንያቱም ነፃ ስለሆነ

ክትባቱ ለሁሉም U.S. ለሚኖር ሰው ካለምንም ወጪ ይቀርባል (ምንም እንኳን አንዳንድ አገልግሎት ሰጪዎች የአስተዳደራዊ ክፍያዎች ቢያስከፍሉም) ከጊዜ በኋላም በተለያዩ አከባቢዎች የመጀመሪያ እርዳታ ሰጪዎችን፣የህዝብ የጤና ክሊኒኮችን እና ፋርማሲዎችን ጨምሮ ክትባቱን ማግኘት የሚፈልጉ ማናቸውም ሰዎች እንዲያገኙት ይደረጋል።

## ምክንያቱም ማንኛውም በእርስዎ አከባቢ ያለ ሰው ደህንነቱ ይጠበቃል

ወጣቶች ወይም ጤናማ ሰዎች ከባድ የሆነ ህመም የመያዛቸው ስጋት ዝቅተኛ ስለሆነ ክትባቱ አያስፈልገኝም ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። እርስዎ በበሽታው ከተያዙ ሌሎች ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን ለበሽታው ሊያጋልጡ ይችላሉ፤ስለዚህም መከተብዎ የሚወዱዋቸውን ሰዎች፣የስራ አጋርዎችዎን እና ጎረቤትዎን ለመከላከል የሚረዳ አዎንታዊ የሆነ ሞገዳዊ ውጤት አለው።

## ምክንያቱም የወረርሽኙ መቆም በአብዛኞቻችን መከተብ ላይ ስለሚወሰን

ባለሙያዎች እስካሁን ድረስ የመንጋ የመከላከል አቅም እንዲመጣ ምን ያህል ፐርሰንቴጅ የበሽታ የመከላከል አቅም ያላቸው መሆን እንዳለባቸው አላወቁም፤ይህ ደረጃ ማለት ብዙ ሰዎች ከመጠበቃቸው የተነሳ ቫይረሱ መስፋፋት የማይችልበት ሁኔታ ማለት ነው። ነገር ግን ካለ ሰፋ ያለ ክትባት ይሄንን ደረጃ መድረስ አመታት ሊፈጅ ስለሚችል ተጨማሪ ብዛት ያላቸውን ሞቶች ያስከትላል።



## ምክንያቱም የኮቪድ-19 ክትባት ቫይረሱን ብቻ ሳይሆን ከዛ በላይ ስለሚከላከል

ወረርሽኙ በተለያየ የህይወት ገፆቻችን ላይ ጉዳት አድርሷል። ሰፋ ያለ ክትባት እንደ ስራ አጥነት፣የመኖርያ ቤት ማጣት፣ብቸኝነት እና የሱስ መድሃኒቶች ከመጠን በላይ መውሰድን ያሉ የወረርሽኙ ተፅእኖችንም ይዋጋል። ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለሱ፣ቤተሰቦች ወደ መረጋጋት እንዲመለሱ እና የሁከት ስጋቶች እንዲቀንሱ ይረዳል። በዚህም ምክንያት እኛ ጋር ያሉ አዛዉንቶችና ጥቁሮች፣ላቲኖዎች፣ሰነድ አልባዎች እና የጎሳ ማህበረስቦች ጨምሮ በኮቪድ-19 በይበልጥ ለተጎዱት ማህበረሰቦች ይዋጋል።

1.15.21